የሰ/መ/ቁ. 35018

ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- በዛብህ አበበ - ቀረበ፡፡

**ተጠሪ**፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ሕይወት ጥላሁን ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

አከራካሪው ጉዳይ ቀደም ሲል በተሰጠው ውሳኔ መሰረት የተጀመረውን የአፈጻጸም ሂደት የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው የአፈጻጸሙን ክርክር የያዘው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀጠሮው ቀን የፍርድ ባለመብት (የአሁኑ አመልካች) ጠበቃ አልቀረበም በሚል ምክንያት በመስጠት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ይህን ተከትሎ የቀረበለትን የመዝገብ ይከፈትልን ጥያቄም ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም መዝገቡ አይከፈትም በመባሉ የተፈጸመ ስህተት(ጉድለት) የለም ብሏል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አመልካች ጥር 10 ቀን 2000 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የአፈጻጸም መዝገቡ የተዘጋበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ (ትእዛዝ) እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ትእዛዝ የተሰጠበት መዝገብ ቀደም ሲል የተሰጠውን ውሳኔ ለማስፈጸም ሲባል የተከፈተ ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መዝገቡን የዘጋው የፍርድ ባለመብቱ ጠበቃ በቀጠሮው ቀን አልተገኘም በሚል ብቻ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን ለምን ዝም ብሎ አይጠብቅም ነበር ወይም ተለዋጭ ቀጠሮ አይሰጥም ነበር ሊባል ስለማይቻል በመዝጋቱ ረገድ ስህተት ነበር ማለቱ ተገቢ አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች እንደፍርዱ/ውሳኔው/ አልተፈጸመልኝም የሚል እስከሆነ ድረስ መዝገቡ ከነጭራሹ አይከፈትልህም (አይንቀሳቀስም) የሚባልበት የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 384 እንደተደነገገው የአፈፃፀም ጥያቄ እንደገና ለማንቀሳቀስ የማይቻለው በሕጉ እንደተመለከተው በይርጋ ቀሪ ሆኖ ከተገኘ ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ያቀረበው የአፈፃጸም ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሆኗል አልተባለም፡፡ በመሆኑም ያልተፈጸመ ፍርድ አለ እስከተባለ ድረስ መዝገቡ ተከፍቶ አፈጻጸሙ የማይቀጥልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ትእዛዝ ከዚህ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20286 ሰኔ 5 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ እና ይህን ትእዛዝ በማጽናት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57130 ጥቅምት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተከፈተው የአፈፃጸም መዝገብ ተከፍቶ(ተንቀሳቅሶ) አፈጻጸሙ ይቀጥል በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ